# ምድብ አራት (ከ7ኛ — 9ኛ) ክፍል
## 30 ኛ ሳምንት
## ልደታ ለማርያም

**ዓላማ**

- ስለድንግል ማርያም የተነገረ ትንቢት፣የታየ ሕልምና የልደትዋንም ታሪክ መማር።

**የሚጠና ጥቅስ**

- ***"ከሴቶች ሁሉ ተለይተሽ አንቺ የተባረክሽ ነሽ"*** *ሉቃ*.1÷28

**ምንባብ**

- ግንቦት 1 ሳንክሣር እና ነገረ ማርያም።

**መግቢያ**

- ዛሬ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ እናት ድንግል ማርያም የልደት ታሪክ እንማራለን እግዚአብሔር በቅድስናና ንጽሕናዋ እናቱ እንዲትሆን መረጣት

**ትምህርቱ**

- በኢየሩሳሌም ባለ ጸጋ የሆኑ ነገር ግን ንብረታቸውን የሚወርስ ልጅ ያልነበራቸው ባልና ሚስት ነበሩ።እግዚአብሔርን የሚፈሩ ነበሩና ልጅ እንዲሠጣቸው ዘወትር ይጸልዩ ነበር።
- አንድ ቀን ላም ልጅ ስትወልድ የተወለደችዋም ሴላ እየወለደች ስድስት ትውልድ ከደረሰ በኋላ። ስድስተኛዋ ጨረቃ ስትወልድ፣ ጨረቃዋም ፀሐይ ስትወልድ በሕልም አዩ።
- እንደ ዮሴፍ ሕልም ወደሚተርጉም ሰው ሄደው ያዩትን ሕልም ነገሩት።ልጅ እንደሚያገኙ እና እስከ 6 ትውልድ እንደሚሄድ ከዚያም፣በስድስተኛው ትውልዳቸውም የምትወለድ ታላቅ ልጅ እንዳለች የጨረቃዋን ምሳሌ ከተረጎመላቸው በኋላ ፀሐይ ምን እንደሆነ መተርጎም እንዳልቻለ ነገራቸው።
- ጥንዶቹም ሕልም ተርጓሚው እንደነገራቸው እስከ 6 ትውልድ ልጆችና ቤተሰቦችን ተወለዱላቸው።የስድስተኛው ትውልድም ሐና ትባላለች።
- ቤተሰቦችዋም ኢያቄም ለተባለ መልካም ሰው አጭዋት።እያቄም እና ሐና አብረው ለረጅም ጊዜ ኖሩ።ልጅ ሳይወልዱም አረጁ።
- ሐና እና እያቄም ድሆችን የሚረዱና ለእግዚአብሔር ትዕዛዝም ታማኞች ነበሩ። ተስፋ ሳይቆርጡ ወደ በመጸለያቸው እግዚአብሔር ጸሎታቸውን ሰምቶ መልአኩን ወደ ኢየቄም ላከ።
- የእግዚአብሔር መልአክ ለኢያቄም ተገልጾ ውድ ልጅ እንደሚሠጣቸው አበሠረው ኢያቄም ለሐና ነገራት ሐናም በእምነት ተቀብላ እና እምና ትኖር ነበር።
- ሁለቱም በሕልም ተረድተውም ሐና ጸነሠች።የመውለጃዋ ጊዜዋ አልፎ ስለጸነሠችም ዘመዶችዋ ተደነቁ። ሐና አንድ ዓይና አክስት ነበረቻት። አንድ ቀን ሐና መጸነስዋን ስምታ ሆድዋን በእጅዋ ደስሳ ካረጋገጠች በኋላ ዓይኗን በዚያው እጅዋ ስትነካው ዓይንዋ በራላት።
- ሌሎች ሰዎች ይሄን ተዓምር ሰምተው በመምጣት በተዓምር ተፈወሱ። ነገር ግን አይሁድ ቀንተው ሐና እና ኢያቄም እንዲሠደዱ አደረጉ።
- ወደ ሊባኖስ ተራራም ተሠደዱ።በዚያም ግንቦት 1 ቀን ሐና ቆንጆዋንና ተወዳጅዋን ልጅ ወለደች ስምዋንም ማርያም አለቻት።
- እንደስለታቸውም ድንግል ማርያም እስከ 15 ዓመትዋ በቤተመቅደስ እያገለገለች ኖረች።
- እግዚአብሔርም በቅድስና ኖረው በንጽህና ከወለድዋት ልጃቸው ድንግል ማርያም ተወልዶ ዓለምን ለማዳን ፍቃዱ ሆኖ መረጣት።

**መዝሙር**

ምስራቀ ምስራቃት ሙዕዓ ፀሐይ
እግዝእትነ ዘመና ሙዳይ
ዘመና ሙዳይ ማርያም ዘመና ሙዳይ

**ጥያቄዎች**:-

1.የእመቤታችን ቅደመ አያቶች ሕልም ምን ነበር?
2.ሐና እመቤታችን ስትጸንስ ምን ዓይነት ተዓምር ተከሰተ
3.ድንግል ማርያም የት ተወለደች? ለምንስ ወደዚያ ሄዱ?
4.በስተእርጅናው ልጅ እንዲሚወልድ ኢያቄምን የነገረው ማነው?
5.በታሪኩ በጨረቃና በፀሐይ የተመሰሉት ማንና ማን ናቸው?

**ማጠቃለያ**

1. ዳዊት ***"መሠረቶችዋ በተቀደሱ ተራሮች ነው"*** እንዳለ መዝ.86(7)፣1 የድንግል ማርያም ቤተሰቦች እንደ አብርሐምና ይስሐቅ በእምነት የኖሩ ናቸው።በዚህም በትዕግሥትና በመተማመን ጸንተው መልካም ፍሬ ተቀብለዋል።
2. ንጉሡ ሰለሞንም እንደተናገረው እመቤታችን ድንግል ማርያም ***"ለወለደቻት እንዲት ናት"*** መኃ. ነገር ግን ከቤተሰቦችዋ አልፋ ለዓለም ሁሉ የምትተርፍ ንጽሕትና ቅድስት የሆነች የበረከት ልጅ ነበረች።
3. ሰዎች ባልተረዱት ነገር ሲተቹን በጸሎት እና በትዕግሥት መልካምነታችን አጽንተን እንቀጥል፣እግዚአብሔር ይታደገናልና።ሐና እና
ኢያቄም ተስፋ ሳይቆርጡ በእምነት ስለኖሩ ነው እመቤታችንን ያህል በረከት የተቀበሉት።

**ይቆየን።**